

# መድህን ግሱ

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*የካት 18 ቀን 2001 ዓ.ም.*

እያለህ ይሰማኛል
መንፈስህ ይጠራኛል።

ገፅህም ይታዬኛል
ቁጭ ብሎም ያዋዬኛል።

ልይዘው ሰል
ያያያ ... መልጠኛል።

ያሞኘኛል ያታልለኛል
ልጠጋው ሰል ይሸሸኛል።

እንደገና ይታየኛል
ልይዘው ስል ይሾልከኛል።

እንኪ ፀጋ ይለኛል
እንደገና ያባብለኛል።

መንፈስ ሰዶ የዋየኛል
ቃሉን ልኮ አድኖኛል።

መድህን ሆኖ ያፅናናኛል
ህይወት ሆኖ ያፈካኛል።

መንገድ ሆኖ ይመራኛል
ጥበብ ሆኖ ሰጥቶ ይከበኛል።

መክሊት ሆኖ ይረዳኛል
ቃና ሆኖ ይጥመኛል።

መካር ሆኖ ያግዘኛል
ተስፋ ሆኖ ያባብለኛል።

ምርኩዝ ሆኖ ደግፎኛል
ጥላ ሰዶ ከልሎኛል።

ጥግም ሆኖ ገንብቶኛል
ተስፋ ቢስን ገድሎልኛል።

ቀልም ልኮ አቅልሞኛል
ፀበል ልኮ አጥምቆኛል።

ሥርዬት ልኮ ፈውሶኛል
ዕድምተኛ አድርጎኛል።

ጥበብ እሱ .. እሱ በሱ
እሱ ... ነፍሱሱሱ

ጥበብን ሰሱሱሱሱሱሱሱ
ቅዱስ ፀጋ ነው መንፈሱ

ፀጋ አልብብብብ .. ሱ
መድህን ግሱሱሱ .. ሱ

**ሆቴል ሂርሽን ታህሣሥ 11 ቀን 2001 ዓ.ም.**
**መታስብያነቱ ለብላቴ ግታ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድኅን**